# ሶስተኛው የክህደት መንገድ

በልጅግ አሊ

ሰሞኑን የአሜሪካን ሬድዮ ሶስት የታወቁ ግለሰቦቸች ቃለመጠይቅ አሰምቶአል።ልደቱ በኢትዮጵያ ህዝብ አጠራር ክህደቱ ሶስተኛ መንገድ በማለት አዲስ ስልት ቀይሻለሁ ይህም ከኢትዮጵያ ህዝብ ያስታርቀኛል ብሎ ያቀረበውን ሰነድ በሚመለከት የቀረበ ቃለ መጠይቅ ነው። ለኔ ብዙም የተቀየረ አቋም በመድህን ኢ.ደ.ፓ ሶስተኛ መንገድ ላይ አላየሁም።ነገር ግን አዲሱ የነልደቱ ሶስተኛው መንገድ የሚያሳየን ሰሞኑን በተደጋጋሚ በአዲስ መልክ ወያኔ አንቀላፊዎቹን(Sleepers) እየቀሰቀሰ መሆኑን ነው ።

አዲስ ያየሁት ነገር ቢኖር አቶ ክህደቱ ቆጣ ቆጣ ማለቱን በጣም የጨመረ ሲሆን እንዲህ ውጭ አገር ያሉትን ለማስፈራራት የሞከረ በኢትዮጵያማ እሱን የሚቃወሙትን ምን እንደሚያደርጋቸው መገመት ይችላል። የማይጋባ ስብራት ብቻ ነው ይሉ ነበር የአንድ ጓደኛዬ እናት ክህደቱን ውሎው ከወያኔ ከባለስልጣን ስለሆነ የተቃወማቸውን ሁላ መቆጣት፣ማሰር ፣ መግደል፣ ከለመዱ ወያኔ ጓደኞቹ ይህ ቁጣ ስለታጋባበት ሌሎቹን ቃለመጠይቅ ተደራጊዎችንና ጋዜጠኛውን በቁጣ ዝም ሊያሰኛቸው ሞክሮዋል። ጓደኞቹ ወያኔዎች ነፃውን ፕረስ እንዳፈኑ ልደቱም ያለ የለለ ሃይሉን ተጠቅሞ የአሜሪካን ሬዲዮ ጋዜጠኛ ቃላት እየሰነጠቀ ጥያቄ እንዳይጠይቀው ለማድረግ ያደረገው ሙከራ በጋዜጠኛው ከሽፎበታል።

አቶ ብርሃኑ መዋ በአንዳንድ አቋማቸው ባልስማማ እንኳ በዚህኛው ቃለ መጠይቅ ላይ ታሪክ ያጣቀሰ አባባላቸውን ጥሩና የበላይነት ያሳዩበት ነውና ሳላደንቅ አላልፍም። እንደውነቱ ከሆን መቶ አለቃ አያልሰው ቃለ መጠይቁ ስለምን እንደነበረ ያወቁ አይመስሉም ወይም ወዴት እንደሚሄድ አልተረዱትም። ነፍስ ይዞአቸው ህብረቱን አንድ ግዜ ለመከላከል ያደረጉት ጥረት እንደ የዋህ ፓለቲከኛ ነው ያሳያቸው። አንድ በልባቸው ያለና የቆየ አሳብ ነው ያቀረቡት።ግለሰቡ የገለፁት የሰላሳ አመቱን ትግል ለመውቀስና አዲስ የትግል ዘዴ ከአራት አመት በፊት መቀየሳቸውን ነው ። በዚህም ሳያውቁት ልደቱ ወጥመድ ውስጥ ስለገቡለት ያንን በመጠቀም እሳቸውን እንደ ጥሩ ብርሃኑ መዋን እንዳራዊት እያደረገ ከወያኔ በተሰጠው መመሪያ ተቃዋሚውን ጎራ ለመከፋፈል ጥረት አድርጎአል።እዚህ ላይ ነው ልደቱ ግዜውን ጠብቆ ከተኛበት እንዲንቀሳቀስ የተደረገ የወያኔ አንቀላፊነቱ የተጋለጠው። ይህቺ ነች እንግዲህ የወያኔ አንቀላፊ(ስሊፐር) ጠባይ።

እውን የመድህን ኢ.ደ.ባ ሶስተኛ መንገድ አዲስ ነው ? ወይስ እነዛው የፈረደባቸውን ቅን አንጃቶች ወደ ወያኔ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት? እውን ልደቱ በተቃዋሚው ጎራ ነው ወይስ በወያኔ? አዲሱ ሶሰተኛ መንገድ ማለት ምንድነው?

ዛሬ ልደቱም ሆነ መሰሎቹ ማንንም ተቃዋሚ ነን ብለው ሊያታልሉ አይችሉም። ተቃዋሚም አደሉም።በቀጥታ ከመንግሰት ትህዛዝ እየተሰጣቸው የሚንቀሳቀሱ የወያኔ አንቀላፊዎች ናቸው።የሶስተኛው መንገድ ታላቅ ሚሰጥር አንዳንድ ለእነርሱ የሚታያቸውን መልካም ስራ እያነሳን ወያኔን እናወደስ ነው የሚሉን። መድህን ኢ.ደ.ፓ ወያኔን ከማወደስ ወደ ኋላ ብሎም አያውቅም። በዚህ በሶስተኛው መንገድ የሚጠየቀው ግን ሌሎች ተቃዋሚዎችን እንደኛ ለወያኔ እደሩ ነው።እነልደቱ የተቃዋሚ ወገኖችን ህብረቱም ሆነ ቅንጅትን ወያኔን አትቃወሙን ብለው መጠየቅ አይችሉም።ዋናው ግን ሊመረምሩት የሚገባው መድህን ኢ.ደ.ፓ ወያኔን በሚገባ ተቃውመናል ወይ ነው። ለይስሙላ አንዳንድ ቃላት መግለጫቸው ውስጥ መክተት ተቃዋሚነታቸውን አያሳይም።

ልደቱ የወያኔ አንቀላፊነቱን ለማወቅ ከአንድ ቃለ መጠይቅ ሊያልፍ አልቻለም። ከወያኔ የተላከበት አላማው ተቃዋሚዎችን መከፋፈል መሆኑን ለመረዳት ያነሳቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ምስክር ናቸው። እስቲ የወያኔ መልካም ስራዎች ተብለው በመድህን ኢ.ደ.ፓ የሚጠቀሰዉን እንመልከት።

- እነ ልደቱ የተከፈተ ቡና ቤትን እየቆጠሩ የሃገሪቱን እድገት ተመልክቱና አድንቁ ነው የሚሉን።
- ልደቱ ለነፃነት ሲሉ ስለሞቱት ወጣቶች እርሱና ስለበለፀጉት የወያኔ ሃብታሞች ብቻ አውሩ ነው የሚለን።
- የታሰሩትን የቅንጅትና የኢሕአፓ አባላት ትታችሁ ፓራላማ ለገባነው ስገዱ ነው የሚለን።
- የልደቱ ሶስተኛ መንገድ ውሃ በፈረቃ መታደሉን ሳታነሱ ሸራተን ስለሚቀዳው ውስኪ አድንቁ ነው የሚለን።
- የመድህን ኢ.ደ.ፓ አዲሱ የትግል ስልት የሚያደርገው ጫማ የሌለውን የሃገሪቱን ወጣት ሳታነሱ አዲስ የበቀለውን ሃብታም የሚይዘውን መኪና ተመልከቱ ነው የሚለን።
- ክደቱ ነፃው ፕረስ ማለታችሁን ትታችሁ ሪፖርተርን እና መሰሎቹን አንብቡ ነው የሚልን ።
- ደብተራውን ፣ ኢትዮኢንዴክስን ወዘተ ትታችሁ ዐይጋ ፎሩም አድንቁ ነው የሚለን።
- ልደቱ እመንገድ የሚድረውን ትታችሁ ከውጭ አገር መሬት የተመራውን አስቡት ነው የሚለን።
- ክህደቱ የግቦቱን ድል ተውና ወያኔ ሶማልያ ወስጥ ያገኘውን ድል አድንቁ ነው የሚለን።
- ልደቱ የተራበውን ስው ትታችሁ እኛ የምንበላውን ኬክ ተመልከቱት ነው የሚለን ።
- በብዙ የሚቆጠረውን ስራ አጥ ወጣት እረስታችሁ ለወያኔ በማደር የተጠቀምነው ፓለቲከኞች ተመልከቱን ነው የሚለን።
- በሚሌኒየሙ በአል አንድ ኪሎ ስጋ መግዛት የማይችለውን ትታችሁ በትልልቁ ቡና ቤት ውሰጥ የሚጨፍረውን ተመልከቱት ነው የሚለን።
- 25 ኪሎ ስንዴ በቤተሰብ የሚታደውን ትታችሁ ሁል ግዜ ከውጭ አገር እየተገዛ የሚመጣ ምግብ የሚበላውን ነው አድንቁ የሚለን።

ልደቱ እነዚህን በተመለከቱ ነው ጭፍን ተቃውሞን እናቁምና የወያኔን መልካም ጎን እናውጋ የሚለው።

የልደቱ ሶስተኛ መንገድ ለኔ የጨለማ ጉዞ ነው። መደናበር ነው ፣ መታወር ነው።ጭፍን ወያኔን መደገፍ ነው።በአድርባይነቱ ከህብረተሰቡ የተነጠለ ብቸኛ ፍጡር የሚያደርገው መፈራገጥ ነው። የሚተርፈው ነገር ስለሌለ እራስን ከመላላጥ አያልፍም ። በምንም አይነት ልደቱ እንደተቃዋሚ ሊወሰድ አይችልም። ልደቱ ወያኔ እንጂ ተቃዋሚ አደለም። ልደቱ በአካባቢው የከበቡትን የወቅቱ የወያኔ ከበርቴዎች በፈለጉት ጊዜ የሚቀሰቅሱት የሚንቀሳቀስ የወያኔ አሻንጉሊት ነው።ልደቱ ዛሬ ከጠፋበት ተመልሶ እሱን ተከትለን ወያኔን እንድንደግፍ ያቀረበልን አሳብ ወያኔ ይሰራልኛል ብሎ በራሱ ሚዲያ ሲያውጅ ከነበረው የአገሪቱ ኢኮኖሚ አደገ ተመነደገ ከሚለው የተለየ ስላልሆነ አሁን አይሰራም።

**ድሮ አገራችን ሳለን የነበረብን የእንግሊዘኛ መፀሀፍ እጥረት የማልረሳው ነው።ያም ሆኖ አሮጌ መፀሀፍ የሚሸጥበት መርካቶ ከወጣን ብዙ ግዜ አንድ እራምፓ(Lobsang Rampa) የሚባል የትቤት በኃላ እንግሊዛዊ ሆኖ የተገኘ ሰው መፀሀፍ ይሸጥ ነበር። ከመጻህፍቶቹ ሁሉ ሶስተኛው አይን(The Third Eye) የሚል መፀሐፍ ትዝ ይለኛል። Rampa በዚህ መፀሀፉ የጠቀሰው አይን በግንባሩ ላይ አስተከልኩ ብሎ ነው የፃፈው። ይህ አይን እንደሱ አባባል**(A third eye is drilled into his forehead, allowing him to see human auras and to determine people's hidden motivations.) **የተደበቀውን የሰው ፍላጎት የሚያይበት ነው። ይህንን ዛሬ እዚህ ያመጣሁት ተቃዋሚዎች ሶስተኛ መንገድ ሳይሆን ሶስተኛ አይን ነው የሚስፈልጋቸው ። በየጊዜው የሚቀሰቀሱትን የወያኔ ቅጥረኞች ጉዳት ከማምጣታቸው በፊት ሊጋለጡ የሚችሉበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል። ልደቱ ግልፅ የወጣ ነው። ግን ደግሞ ወደፊት አዳዲሶች የተደበቁና ግልፅ ያልወጡ ሊመጡ ስለሚችሉ ነቅቶ መጠበቅ ያሻል።እያንዳንዳችን ሶሰተኛ አይናችንን እንክፈት።**

**በልጂግ አሊ**